EthioLion

# የመከራው ፅዋ

አገሬ ከስዊድን ነሐሴ 2011

ኢትዮጵያ ሀገሬ ፤  የወለድ መካን
አንችን እየካደ ፤  መጥቶ ሲገዛን
በጨካኜው ብዛት ፤  ስንበታተን
በየደረስንበት ፤  ሞት አሸነፈን
የመከራው ፅዋ ፤  በየቤቱ ገብቶ
ተሰዶ ተግዞ ፤  ተርቦ ተጠምቶ
አለቀ ወገኔ ፤  አይሞቱ ሞት ሞቶ
ሞትም ክብር ነስቶን ፤  እያሽመደመደ
በውርደት ጨረሰን ፤  አገር እያስካደ
አይን አላይም አይል ፤  ጆሮ አይል አይሰማ
ዛሬም ወገን ሲራብ ፤  ሲቆስል ሲደማ
በአለም ተበትኖ ፤  ሮሮ ሲያሰማ
በየደረስንበት ፤  ያለው እንግልት
ማለቂያ የለውም፤  ቢፃፍ ቢታተት
ኢትዮጵያዊው ቆሞ ፤  በፈተና ማማ
መከራውን ሲጋት ፤  ዛሬም ሳያቅማማ
አደባባይ ወጥቶ ፤  በአለም ተሰማ
ውዷ ኢትዮጵያዊ ፤  እህቴ ውቢቷ
ኑሮ ባይሆንላት ፤  ባገሯ በቤቷ
መቋቋም ቢያቅታት ፤  የሀገሯን ፍዳ
ተሰዳ ወደቀች ፤  በአረብ ምድረበዳ
ታስራ ተጠፍራ ፤  እጅ እግሯ ተይዞ
አፏ ተለጉሞ ፤  ለመከራው ጉዞ
በሊቢያ ጭራቅ ፤  የምድረበዳዋ
በዛች የሴት አውሬ ፤  ጨካኝ ሰው በላዋ
ውቧ የአገሬ ልጅ ፤  ፈረሰ ገላዋ
በአርብ ቤተመንግስት ፤  ያልፍልኛል ብላ
ዉቢቷ እህታችን ፤  አየን ተቀቅላ
አረመኔዋ ሴት ፡  ጭራቅ ተመስላ
ውድ እህታችንን ፤  ከነነፍሷ ጥላ
እንደፈለገችው ፤ ጎንፋ ቀቅላ
አውሬው ባህሪዋ ፤ አልረካም ቢላት
ላትጠጣ ላትበላ ፤  ሀኪም ላያያት
ህግ አስተላለፈች ፤  በቤተመንግስት
ሰይጣን በሴት ጭራቅ ፤  ታዞ ተመስሎ
በቤተመንግሰቱ ፤  ሲታይ ተስተውሎ
ሀዘኔ በረታ ፤  በእህቶቸ ፍዳ
በሌሎቹ ውሎ ፤  በየአረቡ ጓዳ
እንደኔማ ቤሆን ፤  በእኔ ፍላጎት
ቀን እስኪያልፍ ብሎ ፤  በአረብ መገዛት
እርም ነው ደይን ነው፤  ሀራም ነው ቢሉት
ፀጋ ይሆን ነበር፤  በሀገር መሞት
እርሀብ እርዛት ፤  ጭቆናና አድልኦ
ባገር ላይ ሲፈፀም ፤  ቢያሰኝም እግዚኦ
ላይቀርልን ፍዳ ፤  ይህ ሁሉ ማነቆ
መከራና ስቃይ ፤  መኖር ተሸማቆ
ነፃነት መሞት ፤  በአገር ላይ ተዋድቆ
ክብር ይመስለኛል ፤  የወገን ኩራት
ለመብቱ ተሟግቶ ፤  በሀገር መሞት።

EthioLion.com

Ethiopia Will Prevail!